## Chapter 1

### Exericse 3

**CD 1**

a

ሴት: ስምህ ማን ነው?
ወንድ ስሜ ገብረስላሴ ገብረማርያም ነው።
ሴት ይቅርታ ማን አልከኝ?
ወንድ ገብረስላሴ ገብረማርያም፣ ስሜ ገብረስላሴ ገብረማርያምነው።
ሴት እሺ።

**CD 2**

b

ሴት 1 ስምሽ ማን ነው?
ሴት 2 ስሜ መቅደስ ማሞ ይባላል።
ሴት 1 ይቅርታ ማን አልሽኝ?
ሴት 2 መቅደስ ማሞ ፤ ስሜ መቅደስ ማሞ ይባላል።
ሴት 1 እሺ አመሰግናለሁ።

**CD 3**

c

ሴት ታድያስ! ማን ትባላለህ?
ወንድ ጀምበሩ ደስታ እባላለሁ።
ሴት ይቅርታ ማን አለክኝ?
ወንድ ጀምበሩ ደስታ ። ጀምበሩ ደስታ እባላለሁ።
ሴት 1 እሺ አመሰግናለሁ።

**CD 4**

d

ወንድ ሰላም ነው። ማን ትባያለሽ?
ሴት ኢማን መሃመድ እባለለሁ።
ወንድ ይቅርታ ማን አልሽኝ?
ሴት ኢማን መሃመድ እባላለሁ።
ወንድ እሺ። አመሰግናለሁ።

**CD 05**

**Exercise 9a**

ሴት: ስምህ ማን ነው?
ወንድ: ስሜ ሄኖክ ነው። አንቺስ፤ ስምሽ ማን ነው?
ሴት: ሙና እባላለሁ።

**CD 06**

**Exercise 9b**

ወንድ ታድያስ!
ሴት ታድያስ ጴጥሮስ! የመጣኸው ከምን ሃገር ነው?
ወንድ የመጣሁት ከኢትዮጵያ ነው። አንቺስ?

## Chapter 2

### Exericse 6a

**CD 07 a**

ወንድ: ስልክ ቁጥርህ ስንት ስንት ነው?
ወንድ: 00 251 9 22 65 99

**CD 08 b**

ወንድ: ስልክ ቁጥርሽ ስንት ስንት ነው?
ሴት: 00 251 9 71 23 45

**CD 09 c**

ወንድ: ስልክ ቁጥሮት ስንት ስንት ነው?
ሽማግሌ: 00 49 74 25 43 33

**CD 10 d**

ወንድ: ስልክ ቁጥርህ ስንት ስንት ነው?
ሴት: 09 85 11 24 95

### Exericse 6b

**CD 11** a

oo00251 -4 -23 54 32

**CD 12** b

00251 9 90 86 33

**CD 13** c

09 67 73 38 27

**CD 14** d

0913 25 97 89

**CD 15**

**Exericse 12a**

ተማሪ ፣ አስተማሪ፣ ነጋዴ፣ ጸጉር ሰሪ ፣ ጋዜጠኛ ፣ መሃንዲስ፣ አርክቴክት፣ ሃኪም ፣ አስተናጋጅ; ጽዳት ሰራተኛ

**CD 16**

**Exericse 12b**

1 ሴት፡ ተማሪ ነህ?
ወንድ፡ አይ፣ ተማሪ አይደለሁም፤ አስተማሪ ነኝ።

2 ወንድ፡ ነርስ ነሽ?
ሴት፡ አይ ፣ ነርስ አይደለሁም። ሃኪም ነኝ።

3 ወንድ፡ ስራህ ምንድን ነው?
ሴት፡ የሒሳብ ሰራተኛ ነኝ።

4 ወንድ፡ ስራሽ ምንድን ነው?
ሴት፡ አርቲስት ነኝ።

5 ሴት፡ የት ትሰራለህ?
ወንድ፡ ቡና ባንክ እሰራለሁ።

6 ወንድ፡ የት ትሰሪያለሽ?
ሴት፡ ካዲስኮ ሆስፒታል እሰራለሁ።

# Chapter 3

**CD 17**

**Exericse 7a**

1 ይህ ማን ነው?

2 ይቺ ሚስትህ ናት?

3 ባለትዳር ነህ?

4 የባለቤትህ ስም ማን ነው?

5 የባለቤትህ ስም ጽዮን ነው?

6 ስራሽ ምንድን ነው?

**CD 18**

**Exericse 7b and c**

ሴት: ይህ አባትህ ነው?

ወንድ: አይ፣ ይህ አባቴ አይደለም። ይህ አጎቴ ነው።

ሴት: አጎትህ የት ይኖራል? አዲስ አበባ ነው?

ወንድ: አዎ፣ አጎቴ አዲስ አበባ ይኖራል።

ሴት: ባለትዳር ነው?

ወንድ: አይ ባለትዳር አይደለም።

**Exericse 14**

**CD 19**

ጋዜጠኛ፡ ስምሽ ሰላም ሃይሌ፣ እድሜሽ 34፤ የመጣሽው ከምን ሃገር ነው?

ሰላማዊት፡ የመጣሁት ከኤርትራ ነው። ነገር ግን አሁን አዲስ አበባ እኖራለሁ። በአባቴ ኢትዮጵያዊት፣ በእናቴ ደግሞ ኤርትራዊት ነኝ።

ጋዜጠኛ፡ ትግርኛ መናገር ትችያለሽ?

ሰላማዊት፡ አዎ፣ ትግርኛ መናገር እችላለሁ።

ጋዜጠኛ፡ ሌላ ምን ቋንቋ ትናገሪያልሽ?

ሰላማዊት እንሊዝኛ በደንብ፣ ትንሽ ትንሽ ጀርመንኛ እና ፈረንሳይኛ እናገራለሁ።

ጋዜጠኛ፡ ስራሽ ምንድን ነው?

ሰላማዊት፡ የጥርስ ሀኪም ነኝ።

ጋዜጠኛ፡ የት ትሰሪያልሽ

ሰላማዊት፡ አሁን አዲስ አበባ ፣ አንድ የጥርስ ክሊኒክ እሰራለሁ።

ጋዜጠኛ፡ ባለትዳር ነሽ?

ሰላማዊት፡ አዎ፣ ባለትዳር ነኝ። ሁለት ልጅ አለኝ።

ጋዜጠኛ፡ የልጆችሽ ስም ማን ነው?

ሰላማዊት፡ ሴት ልጄ ሄለን ትባላለች፣ ወንድ ልጄ ደግሞ ሳሙኤል ይባላል።

ጋዜጠኛ፡ ልጆችሽ ስንት ዓመታቸው ነው?

ሰላማዊት፡ ሄለን 3 ዓመቷ ነው፣ ሳሙኤል ደግሞ 5 ዓመቱ ነው።

ጋዜጠኛ፡ አመሰግናለሁ።

ሰላማዊት፡ ምንም አይደል።

## kїllӓsa Chapter 1-3

### CD 20

### Exercise 3

የሎተሪ አሸናፊ ቁጥሮች እነዚህ ናቸው። መልካም እድል።
12፣ 48 ፣ 29 ፣ 7፣ 35፣ 16፣

### CD 21

### Exercise 5

~~ሰውዬ፡ ተለማመዱ።~~

ሴትዮ፡ ስራህ ምንድን ነው/ ስራሽ ምንድን ነው?

ሰውዬ፡ ተማሪ ነኝ።

ሰውዬ፡ ስራሽ ምንድን ነው?

ሴት፡ አርክቴክት ነኝ።

ሰውዬ፡ ስራዎት ምንድን ነው?

ሽማግሌ፡ ጋዜጠኛ ነኝ።

ሰውዬ፡ ስራችሁ ምንድን ነው?

ተማሪዎች፡ ተማሪዎች ነን።

ሰውዬ፡ የት ትሰራለህ?

ሴትዮ፡ ኢትዮጵያ አየር መንገድ እሰራለሁ።

### CD 22

### Exercise 6

ሰውዬ፡ የመጣኸው ከምን ሀገር ነው?

ሴትዮ፡ እኔ የመጣሁት ከስፔን ሀገር ነው።

ሰውዬ፡ አንቺስ፣ የመጣሽው ከመን ሀገር ነው?

ሴትዮ፡ የመጣሁት ከፈረንሳይ ነው።

ሴትዮ፡ ስምህ ማን ነው?

ሰውዬ፡ ስሜ ዴቪድ ነው። አንቺስ፤ ስምሽ ማን ነው?

ሴትዮ፡ ስሜ ሱዛና ነው።

ሰውዬ፡ ጤና ይስጥልኝ!

ሴትዮ፡ አብሮ ይስጥልኝ!

ሰውዬ፡ ስምዎት ማን ነው?

ሴትዮ፡ ስሜ መብራት ክንዴ ነው።

ሰውዬ፡ የመጡት ከምን ሀገር ነው?

ሴትዮ፡ የመጣሁት ከኢትዮጵያ ነው።

### CD 23

### Exercise 9

አይ በሉና አሉታዊ ምልስ ስጡ።

ሴትዬ፡ ኤደን ጸጉር ሰሪ ናት? (አስተማሪ)

ሰውዬ፡ አይ፣ ኤደን ጸጉር ሰሪ አይደለችም። አስተማሪ ናት።

ሴትዮ፡ አስቴርና ነብዩ ባለትዳር ናቸው?(ተፋተዋል)

ስውዬ፡ አይ፤ አስቴርና ነብዩ ባለትዳት አይደሉም። ተፋተዋል።

ሴትዮ፡ ካሌብ ብቻውን ይኖራል? (ከሄለን ጋር)

ሰውዬ፡ አይ፣ ካሌብ ብቻውን አይኖርም፤ ከሄለን ጋር ይኖራል።

ሴትዮ፡ ቤርሳና ዳናይት አዲስ አባባ ይኖራሉ? (ጎንደር)

ሰውዬ፡ አይ፣ አዲስ  አባባ አይኖሩም፤ ጎንደር ይኖራሉ።

ሴትዪ፡ ሜሮን 19 አመቷ ነው። (21)

ሰውዬ፡ አይ፣ 19 አመቷ አይደለም። 21 አመቷ ነው።

ሴትዮ፡ ወይዘሮ ጸሀይ አስተማሪ ናቸው።(ጋዜጠኛ)

ሰውዬ፡ አይ፤ ወይዘሮ ፀሀይ አስተማሪ አይደሉም። ጋዜጠኛ ናቸው።

## Fӓtӓna Chapter 1-3

### Exercise 1

### CD 24/1

ሰውዬ 1፡ ሰላም ስይፉ፣ እንደምን ነህ?`

ሰውዬ 2 በጣም ደህና ነኝ። አሁን አማርኛ አስተማሪ ነኝ። በስራዬ ደስተኛ ነኝ። አንተስ እንዴት ነህ?

ሰውዬ 1፡ ምንም አልልም። አሁን ስራ የለኝም።

### CD 25/2

ሴትዮ፡ ጤና ይስጥልኝ!  ስሜ ኤልሳ ንጉሴ ነው።

ሰውዬ፡ አብሮ ይስጥልኝ ወይዘሮ ኤልሳ! የመጡት ከቱርክ ነው?

ሴትዮ፡ አይ፣ አይደለም። ባለቤቴ ነው ከቱርክ የመጣው።

ሰውዬ፡ ቱርክኛ ይናገራሉ?

ሴትዮ፡ ቱርክኛ ትንሽ ትንሽ ብቻ እችላለሁ! እንግሊዝኛና ፈረንሳይኛ ግን በደንብ እናገራለሁ።

**CD 26 / 3**

ሴትዮ፡ ስምህ ማን ነው?

ዮናስ: ዮናስ ማሞ።

ሴትዮ፡ ስንት ዓመትህ ነው፤ ዮናስ?

ዮናስ 15 ዓመቴ!

ሴትዮ፡ እሺ

**CD 27/4**

ሴትዮ 1 ቃልኪዳን፣ ስንት ዓመትሽ ነው? 34 ወይስ 35?

ሴትዮ 2 34 ዓመቴ ነው።

ሴትዮ 1 እህትሽ ስንት ዓመቷ ነው?

ሴትዮ 2 እህቴ 42 ዓመቷ ነው።

**CD 28/ 5**

ሰውዬ 1፡ ሄኖክ ስራህ ምንድን ነው?

ሰውዬ 2፡ ሂሳብ ሰራተኛ ነኝ። ባንክ እሰራለሁ።

ሰውዬ 1፡ ምን ባንክ ትሰራለህ?

ሰውዬ 2፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እሰራለሁ።

**CD 29 /6**

ሰውዬ 1 ፡ ስምዎት ማን ነው?

ሰውዬ 2 ፡ ስሜ አስራት ሞላ ነው።

**CD 30/7**

ሴትዮ 1 ፡ ወይዘሮ ሙሉ፤ ስልክ ቁጥርዎ ስንት ስንት ነው?

ሴትዮ 2 ፡ 0932 23 64 87

**CD 31**

**Exercise 4b**

1 ታድያስ! ስሜ ማርያም ነው። አንተስ, ስምህ ማን ነው?/አንቺስ ስምሽ ማን ነው?

2 የመጣሁት ከስፔን ሀገር ነው። አንተስ፤ የመጣኸው ከምን ሀገር ነው?/አንቺስ የመጣሽው ከመን ሀገር ነው?

3 እኔ ጎንደር እኖራለሁ። አንተስ የት ትኖራለህ?/አንቺስ የት ትኖሪያለሽ?

4 ሃኪም ነኝ። አንተስ፣ ስራህ ምንድን ነው?/አንቺስ ስራሽ ምንድን ነው?

5 ባለትዳር ነኝ። ነገር ግን ለጅ የለኝም። አንተስ፤ ባለትዳር ነህ/አንቺስ፤ ባለትዳር ነሽ?

6 አማርኛ እና እንጊዝኛ እናገራለሁ። አንተስ፤አማርኛ ትናገራለህ/አንቺስ፤አማርኛ ትናገሪያለሽ?

## Chapter 4

**CD 32**

**Exercise 9**

100, 200, 300, 400, 500, 600, 700, 800, 900, 1000, 1010, 910, 920, 930, 940, 950, 960, 970, 980, 1080, 1090, 990, 890, 790, 690, 590, 580, 680, 780, 670, 760, 650, 740, 630, 720, 610, 510, 410, 310, 210, 110, 100

**Exercise 11**

**CD 33 /a**

ሰውዬ፡ ወንበሩ በጣም ያምራል!

ሴትዮ፡ ዋጋው ስንት ነው?

ሰውዬ፡ ወንበሩ 970 ብር ነው።

**CD 34 /b**

ሴትዮ፡ ይቅርታ!

ነጋዴ፡ አቤት። ምን ልርዳሽ?

ሴትዮ፡ ምንጣፉ ስንት ነው?

ነጋዴ፡ ምንጣፉ። 64 200 ብር ነው።

ሴትዮ፡ ምን እንዴ! በጣም ውድ ነው!

**CD 35 /c**

ሴትዮ፡ እዚህ ጋ ተመልከቺ!። የራስጌው መብራት 400 ብር ብቻ ነው።

ሰውዬ፡ ዎው 400 ብር ብቻ። ርካሽ ነው።

**CD 36 /d**

ነጋዴ፡ ምን ልርዳዎት?

ገዢ፡ ይህ መደርደሪያ ስንት ነው?

ነጋዴ፡ እድለኛ ነዎት። አሁን ልዩ ቅናሽ ላይ ነን። የመደርደሪያው ዋጋ 2100 ብር ብቻ ነው።

ገዢ፡ ዎው። 2100 ብር ብቻ! ጥሩ ዋጋ ነው።

**CD 37**

**Exercise 12**

a የመብራቱ ዋጋ 950 ብር ብቻ ነው።

b ምንጣፉ 850 ብር ብቻ ነው።

c. ወንበሩ 972 ብር ብቻ ነው።

d ስዕሉ 644 ብር ብቻ ነው።

e ጠረጴዛው 1286 ብር ነው።

**Exercise 15**

**CD 38**

ኤደን፡ ሳሚ!
ሳሚ፡ ወዬ!
ኤደን፡ እዚጋ ቁምሳጥኑን ተመልከት! በጣም ቆንጆ ነው።
ሳሚ፡ ምንም አይልም። ቁም ሳጥኑ በጣም ትልቅ ነው።
ኤደን፡ ኧረ ትልቅ አይደልም።
ሳሚ፡ ዋጋው ስንት ነው?
ኤደን፡ እዚጋ ዋጋው የለም።
ይቅርታ!
ሳሚ፡ እኔ ሳጥኑን አልወደድኩትም!
ሻጭ፡ ሰላም። ምን ልርዳቻሁ?
ኤደን፡ ቁም ሳጥኑ ዋጋው ስንት ነው?
ሻጭ፡ ቁም ሳጥኑ 25 000 ብር ነው።
ሳሚ፡ 25 000 ብር። በጣም ውድ ነው።
ሻጭ፡ አይ፣ ጥሩ ዋጋ ነው። ጥራት ያለው እቃ ነው።
ሳሚ፡ ቢሆንም።
ኤደን፡ ሳሚ። ቁም ሳጥኑ ቆንጆ ነው። ዋጋውም ውድ አይደለም።
ሳሚ፡ እኔንጃ

**CD 39**

**Exercise 16a**

1 ግን ፣ ጣልያን ዘመናዊ ፣ ምቹ፣ መብራት ፣ ሀገር
2 ኢትዮጵያ፣ በጣም፣ ወንበር፣ አልጋ፣ ምንጣፍ
3 ስንት፣ ትልቅ፣ ጠረጴዛ፣ ክፍል ፣ ቆንጆ
4 ሰፋ፣ ትንሽ፣ ዋጋ፣ ልዩ፣ ቅናሽ
5 በርጩማ፣ ውድ፣ ጥሩ፣ መቶ፣ እናት

**Exercise 16b**

**CD 40**

1 353
2 876
3 1389
4 92 049
5 7 182
6 99 999

## Chapter 5

**CD 41**

**Exercise 14a**

ሴት: ይህ በአማርኛ ምን ይባላል?
ወንድ: ይህ በአማርኛ ጠረጴዛ ይባላል።
ሴት: ይቅርታ ምን አልከኝ? ጠረጴዛ?
ወንድ: አዎ፣ ጠረጴዛ።
ሴት: እሺ። በጣም አመሰግናለሁ።
ወንድ: ምንም አይደል!

**CD 42**

**Exercise 14b**

ወንድ: ይህ በአማርኛ ምን ይባላል?
ሴት: ይህ በአማርኛ ዛፍ ይባላል።
ወንድ: ይቅርታ ምን አልከኝ? ዛፍ?
ሴት: አዎ፤ ዛፍ።
ወንድ: እሺ፤ አመሰግናለሁ።
ሴት: ችግር የለም።

**Exercise 16**

**CD 43**

1 ሰላም ሄለን፤
የዳጊ ልደት ነገ ነው። ስለዚህ ስጦታ መስጠት እንፈልጋለን። አሁን አንድ የስጦታ መሸጫ ሱቅ ነኝ። የኪስ ቦርሳ፤ ሰዓት ወይም ስካርፍ ለመግዛት አስቤያለሁ። ምን ይመስልሻል?

2 ሰላም ዳጊ፤
ጥሩ ሀሳብ ነው። የኪስ ቦርሳ አሪፍ ነው። የዳጊ የኪስ ቦርሳ በጣም አሮጌ ነው።

3 እሺ እዚህ ቆንጆ ቆንጆ የኪስ ቦርሳ በተለያየ ከለር አለ። በምን ከለር ይሁን?

4 ቡኒ ከለር ይወዳል። ስለዚህ በቡኒ ከለር ይሁን።

5 እሺ፤ መልካም 1 ከቆዳ የተሰራ የኪስ ቦርሳ በቡኒ ከለር እገዛለሁ። ዋጋው 1250 ብር ነው።

6 እሺ፤ ጥሩ! እርጠኛ ነኝ። ዳጊ ስጦታውን ይወደዋል።

## Chapter 6
### CD 44
### Exercise 5a and b

1 በር
2 ብር
3 ስም
4 ሰም
5 ቅን
6 ቀን
7 ቻር
8 ስር
9 በግ

### CD 45
### Exercise 9

ደንበኛ፡ ሰላም! ኮምፒተር እና ላፕቶፕ አለ?
ሻጭ፡ ሰላም! እዚህ ታብሌት እና ስልክ አለ።
ደንበኛ፡ እሺ።ጥሩ። እኔ ታብሌት እና ስልክ አያስፈልገኝም።
ሻጭ፡ አሃ ነው እንዴ። ይቅርታ ላፕቶፕ እና ኮምፒተር የለም። ነገር ግን ሞኒተር እና ማውዝ በርካሽ ዋጋ አለ።
ሻጭ፡ አይ። አመሰግናለሁ።ሞኒተርም ማውዝም አልፈግም።

### Exercise 13
### CD 46

ወ/ሮ አስቴር፡ ሳተርን ትሬዲንግ፣ አስቴርን ነኝ። ጤና ይስጥልኝ።

አቶ ተስፋዬ: አብሮ ይስጥልኝ። ስሜ ተስፋዬ ነው። ወይዘሮ ሳራን ማግኘት እችላለሁ።
ወ/ሮ አስቴር፡ አንዴ መስመር ላይ ይጠብቁ።
ወ/ሮ ሳራ: ጤና ይስጥልኝ አቶ ኤርሚያስ። ምን ልርዳዎት?
አቶ ተስፋዬ: አንድ ላፕቶፕ፣ አንድ ስፒከር እና አንድ ኪይቦርድ፣ አንድ ሞኒተር፣ አንድ ታብሌት አስር የኮምፒተር ማውዝ፣ አስራ ሁለት ማርከር፣ አስራ አምስት እስኪብርቶ እና አንድ ካላንደር ፈልገን ነበር።

ወ/ሮ አስቴር፡ እሺ መልካም። አሁን እናደርሳለን። አድራሻዎትን ይነሩናል?

## kïllässa Chapter 4-6
### CD 47
### Exercise 4

ሰውዬ፡ ምን ልርዳዎት?
ሴትዮ፡ ወንበር ፈልጌ ነበር።
ሰውዬ፡ እዚህ ጋር ተመልከቱ። ይህ ቆንጆ ወንበር ነው።
ሴትዮ፡ አዎ፣ ቆንጆ ነው። ዋጋው ስንት ነው?
ሰውዬ፡ 2450 ብር ብቻ ነው። አሁን ታላቅ ቅናሽ ላይ ነን።
ሴትዮ፡ ነው እንዴ! ጥሩ ዋጋ ነው።

### CD 48
### Exercise 6

አዳምጡና ተለማመዱ።
ሴትዮ፡ ጤና ይስጥልኝ! ፀሀይ ደስታ ነኝ። ምን ልርዳዎት?
ሰውዮ፡ አብሮ ይስጥልኝ። ዳንኤል እባላለሁ። .
ሴትዮ፡ ሃሎ። ማን ልበል?
ስውዬ፡ ሃሎ። ከበደ ነኝ። ከኢትዮጵያ ፖስታ ቤት።

### Exercise 8
### CD 49

ሰውዬ፡ አይ ብላችሁ መልሱ።
ሴትዮ፡ ይህ እስኪብርቶ ነው? እርሳስ።
ሰውዬ፡ አይ፣ ይህ እስኪብርቶ አይደለም።እርሳስ ነው።

ሰውዬ፡ ይህ ላይተር ነው? (ክብሪት )
ሴትዮ፡ አይ፣ ይህ ላይተር አይደለም። ይህ ክብሪት ነው።

ሴትዮ፡ ይህ ወንበር ነው? (ሶፋ)
ሰውዬ፡ አይ፤ ይህ ወንበር አይደለም። ይህ ሶፋ ነው።

ሴትዮ፡ ይህ ሻንጣ ነው? (የኪስ ቦርሳ)
ሰውዬ፡ አይ፤ ይህ ሻንጣ አይደለም። ይህ የኪስ ቦርሳ ነው።

**Exercise 10**

**CD 50**

ተለማምደዱ።

ሰውዬ1፡ ደረሰኙ ይኸውልህ!
ሰውዬ2፡ አመሰግናለሁ። ደረሰኙ አያስፈልገኝም።
ሰውዬ1፡ አህ፣ ደረሰኙ አያስፈልግህም።

ሰውዬ፡ ካላንደሩ ይኸውልሽ?
ሴትዮ፡ አመሰግናለሁ። ካላንደሩ አያስፈልገኝም።
ሰውዬ፡ አህ፣ ካላንደሩ አያስፈልገሽም።

ሰውዬ፡ ደብተሩ ይኸውልሽ!
ሴትዮ፡ አመሰግናለሁ። ደብተሩ አያስፈልገንኝም።
ሰውዬ፡ አህ፣ ደብተሩ አያስፈልገሽም።

ሰውዬ1፡ ላፕቶፑ ይኸውልህ!
ሰውዬ2፡ አመሰግናለሁ። ላፕቶፑ አያስፈልገኝም።
ሰውዬ1፡ ላፕቶፑ አያስፈልግህም!

ሰውዬ1፡ ስልኩ ይኸውልህ!
ሰውዬ2፡ አመሰግናለሁ። ስልኩ አያስፈልገኝም።
ሰውዬ1፡ አህ፣ ስልኩ አያስፈልግህም።

**CD 51**

**Exercise 51**

**Fätäna**

**Exercise 3**

**CD 52**

**1**

ሰላም ሄለን፤ አሁን የቤት እቃ መሸጫ ሱቅ ነኝ። እዚህ ቆንጆ ወንበር አለ። የወንበሩ ከለር ሰማያዊ ነው። ብዙም ትልቅ አይደለም። ሰማያዊ ጥሩ ከለር ነው፤ አይደል? አንድ ያልተመቸኝ ነገር፣ ዋጋው ርካሽ አይደለም። በጣም ውድ ነው። እባክሽ አሁኑኑ ደውይለኝ።

**2**

ሰላም ሳራ፣ ሄኖክ ነኝ። አሁን የት ነሽ? እኔ አሁን ቢሮ ነኝ። እዚህ የለሽም። ዛሬ ቀጠሮ ነበረን። አሁን እርቦኛል። ቡና ያስፈልገኛል። አሁን ላፕቶፔን ይዤ ወደ ካፌ እሄዳለሁ። ካፌ ሆኜ እሰራለሁ። አንቺም ወደ ካፌ ትመጫለሽ። እባክሽ አሳውቂኝ።

**3**

ሰላም! እኔና እና ሳራ አዲስ ስልክ ያስፈልገናል። ኦሪጂናል ስልኮች የት መግዛት እንችላለን?

**4**

ሰላም ጤና ይስጥልኝ። ለቢሮ የሚሆን ፕሪንተር አለን። ዋጋው 18 150 ብር ብቻ ነው። የአንድ ዓመት ዋስትና እንሰጣለን።

**5**

ሰላም ዳዊት ፣ ሮዛ ነኝ። ኢንተኔት ኮኔክት ማድረግ አልቻልኩም። ኮፒምፒተሩ የይለፍ ቃሉ ልክ አይደልም ይላል። ፖስፖርዱ አዲስ ነው? የት ነህ?። ዛሬ ከሰዓት 3 ሰዓት ቀጠሮ አለኝ። ኢሜል ያልፈልገልኛል። እባክህ ቢሮ ና።

**6**

ሰላም ማርቆስ ኤልሳ ነኝ። የሆነ ነገር ይታየኛል። ትንሽ ነው። የተሰራው ከወረቀት ነው። ወረቀቱ ላይ ስሜ አድራሻዬ እና የስራ መደቤ አለ።

**7**

ሴትዮ፡ ሳተርን ትሬዲንግ። አሁን እረፍት ላይ ነን። መልዕክት ካለዎት ይተዉ።
ሰውዪ፡ ሰላም ጤና ይስጥልኝ። ዮናስ ነኝ፣ ከታሬ ኮንስትራክሽን። እቃ ማዘዝ ፈልጌ ነበር። 23 አዲስ የቢሮ ወንበሮች፣ 15 በሰማያዊ ከለር፣ ስምንት በግራጫ ከለር። እና አንድ ጠረጴዛ በቡኒ ከለር። ምን አይነት ወንበር አላችሁ። ስልክ ቁጥሬ. . . . 092121....

# Chapter 7

## CD 53

### Exercise 6a

1 ሴት፡ አንተ በደንብ መጋገር ትችላለህ?
ወንድ፡ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።

2 ወንድ፡ አንቺ ጥሩ መዝፈን ትችያለሽ! በጣም ጎበዝ!
ሴት፡ በጣም አመሰግናለሁ።

3 ወንድ፡ አንቺ በደንብ ቴኒስ መጫወት ትችያለሽ!
ሴት፡ ኦህ አመሰግናለሁ።

4 ሴት፡ አንቺ ጊታር መጫወት በደንብ ትችያለሽ!
ወንድ፡ ከልብ አመሰግናለሁ።

## CD 54

### Exercise 8

እችላለሁ።
መጫወት እችላለሁ
ቼዝ መጫወት እችላለሁ
ቼዝ በደንብ መጫወት እችላለሁ።
እኔ ቼዝ በደንብ መጫወት እችላለሁ።

አልችልም።
መንዳት አልችልም።
ብስክሌት መንዳት አልችም።
ከነጭራሹ ብስክሌት መንዳት አልችልም።
እኔ ከነጭራሹ ብስክሌት መንዳት አልችልም።

# Chapter 8

## CD 55

### Exercise 13

1 ነገ ማታ ትችላለህ? / ነገ ማታ ትችያለሽ?

2 አውድ ነገ ማታ እችላለሁ።/ አይ፣ ነገ ማታ አልችም።

3 ነገ ማታ ትችላላችሁ?

4 አዎ፣ ነገ ማታ እንችላለን።/አይ፣ ነገ ማታ አንችልም።

## CD 56

### Exercise 14

### qalä mïlïlïs 1

ሴት: ቅዳሜ ጊዜ አለህ?
ወንድ: ስንት ሰዓት ላይ?
ሴት: ጠዋት አራት ሰዓት ላይ።
ወንድ: አዎ፣ አራት ሰዓት ላይ ጊዜ አለኝ።

## CD 57

### qalä mïlïlïs 2

ወንድ፡ ስንት ሰዓት ነው?
ሴት፡ ለስምንት ሩብ ጉዳይ ነው።
ወንድ፡ ዛሬ ማታ ሲኒማ ቤት እንሂድ?
ሴት፡ አይ፣ ሲኒማ ቤት መሄድ አልፈልግም።

## CD 58

### Exercise 15

ኤደን፡ ሃሎ ማን ልበል?
ሚኪ፡ ማን ልበል። ሚኪ ነኝ!
ኤደን፡ ሰላም ሚኪ እንዴት ነህ?
ሚኪ፡ በጣም ደህና ነኝ። ኤደን፤ ነገ ጊዜ አለሽ እንዴ። እኔና ዳዊት ወደ ሲኒማ ቤት እንሄዳለን። አብረሽን መምጣት ትፈልጊያለሽ?
ኤደን፡ ደስ ይለኛል ነገር ግን ዛሬ ጊዜ የለኝም። ወደ ዋና እሄዳለሁ።
ሚኪ፡ አርብስ? ጊዜ አለሽ?
ኤደን፡ አርብ ጊዜ አለኝ።
ሚኪ፡ ከሰዓት?
ኤደን፡ ይቅርታ ከሰዓት አልችልም። ማታ ከ1 ሰዓት ጀምሮ ጊዜ አለኝ።
ሚኪ፡ ጥሩ። ምናልባት አንድ ላይ ሲኒማ ቤት እንሄዳለን።
ኤደን፡ እሺ። ደስ ይለኛል።

# Chapter 9

## CD 59

### Exercise 14a

1 ሩዝ - ስጋ - ሩዝ በስጋ
2 ቲማቲም - ሾርባ - የቲማቲም ሾርባ
3 ቺዝ - ኬክ - ቺዝ ኬክ
4 ብርቱካን - ጁስ - የብርቱካን ጁስ

## CD 60

### Exercise 14b

አስተናጋጅ፡ ምን ልታዘዝ?
ደንበኛ 1፡ ለኔ አንድ የቲማቲም ሾርባ።
አስተናጋጅ፡ ላንተስ?
ደንበኛ 2: ለኔ አንድ ሩዝ በስጋ።

## ክለሳ Chapter 7-9

### CD 61

### Exercise 3

አዳምጡና በሉ።

ሴትዮ: በደንብ መንደነስ ትችላለህ!

ሰውዬ: ጥሩ መደነስ ትችያለሽ!

ሴትዮ: በደንብ ጊታር መጫወት ትችላለህ!

ሰውዬ: ጥሩ ቴኒስ መጫወት ትችያለሽ!

ሴትዮ: በደንብ መሳል ትችያልለሽ!

ሰውዬ: ዋው ጥሩ ፎቶ ማንሳት ትችላለህ!

### CD 62

### Exercise 5

**አዳምጡና ተለማመዱ።**

ሲኒማ ቤት እንሂድ?

ወይስ ትያትር ቤት እንሂድ?

ዋና እንሂድ?

ወይስ ሙዚየም እንሂድ?

ባር እንሂድ?

ወይስ ምግብ ቤት እንሂድ?

ኮንሰርት እንዲህ?

### CD 63

### Exercise 10

ሰላም! እሺ የሚጠጣ ምን ልታዘዝ?
የሚበላስ?

### Fätäna Chapter 7 - 9

### Exercise 1

### CD 64/1

ራድዮ እንደምን አደራችሁ? ዛሬ ቀኑ እሁድ ነው። የዝግጅቱ አቅራቢ ዮናስ ማሞ ነኝ። ዛሬ ከአዲስ አበባ ጥሩ ጥሩ ሙዚቃ ይዘንላችሁ መጥተናል። አሁን ሰዓቱ ጠዋት 3 ሰዓት ነው። አየሩ ዛሬ በጣም ቆንጆ ነው፤ ሞቃትና ፀሀያማ ነው። በዚህ ቀን ምን ታደርጋላልችሁ። ስልክ ደውሉልን። ስልክ ቁጥራችህን. 011 2 34 53 99 ነው። የመጀመሪያው ሰው መስመር ላይ ገብቷል። ሃሎ! ስምዎትን ማን ልበል።

አድማጭ: ስሜ ኤደን ይባላል።

ራዲዮ: ከየት ነው?

ኤደን: ከአዲስ አበባ ለቡ ነው።

ራዲዮ: ጥሩ። ዛሬ ምን ታደርጊያለሽ

ኤደን: ዛሬ ጠዋት ወደ ቤተክርስያን እሄዳለሁ።

ራዲዮ: ከቤተክርስትያን መልስስ?

ኤደን: 4 ሰዓት ላይ ወደ ዋና እሄዳለሁ። ከሰዓት ቤተሰቤን እጠይቃለሁ።

ራዲዮ: በጣም ጥሩ። ቡዙ ጊዜ ትዋኛለሽ?

ኤደን: አዎ፣ ሁልጊዜ እሁድ እሁድ እዋኛለሁ። ሰኞና እሮብ ጠዋት 1 ሰዓት እዋኛለሁ።
እሺ ጥሩ ። ስለደወልሽ እናመሰግናለን። መልካም ቀን!

### CD 65/2

አሁን ሌላ ሰው መስመር ላይ ነው። ሰላም ጤና ይስልጥኝ። ስምዎትን ማን ልበል?

ሚካኤል: ሜካኤል ነኝ።

ራዲዮ : ከየት ነው?

ሚካኤል: ከአዲስ አበባ ቦሌ ነው።

ራዲዮ : ቦሌ እንዴት ነው?

ሚካኤል: ቦሌ ቆንጆ ነው።

ራዲዮ : ዛሬ ምን ታደጋለህ?

ሚካኤል: ዛሬ ቴኒስ እጫወታላለሁ። ጓደኛዬን አገኛለልሁ። ከጓደኛዬ ጋር ወደ ሰዕል ኤግዚቢሽን እንሄዳለን። ማታ እራት እሰራለሁ።

ራዲዮ : እራት ትሰራለህ? በደንብ ማብሰል ትችላለህ?

ሚካኤል: ምንም አልልም። ጓደኛዬ ግን በደንብ ማብሰል ትችላለች!

ራዲዮ : ምን ታበስላለህ?

ሚካኤል: ምስር እና ጎመን በስጋ።

ራዲዮ : ጥሩ። መልካም ቀን! ስለደወልክ እናመሰግናለን!

### CD 66/3

አሁን ሌላ ሰው መስመር ላይ አለ። አሁን ሳራ መስመር ላይ ናት! ሳራ ስንት ዓመትሽ ነው?

ሳራ: 17 ዓመቴ ነው።

ራዲዮ : ዛሬ ምን ታደርጊያለሽ?

ሳራ: ዛሬ ከሰዓት አስር ሰዓት ተኩል ላይ ኮንሰርት አለ። ኮንሰርቱ ላይ ጊታር እጫወታለሁ።

ራዲዮ : ዎው።ይህ በጣም ደስ ይላል።

ሳራ: አዎ፣ አሪፍ ነው። ከኮንሰርቱ በኋላ ከጓደኞቼ ጋር ወደ ሬስቶራንት እንሄድና በርገርና ቺፕስ እንበላለን።

ራዲዮ : ጥሩ ሀሳብ ነው። እኔም በርገር እና ቺፕስ እወዳለሁ። አድማጮቻችን ስለደዋልችሁ እጅግ በጣም እናመሰግናለን። መልካም ሰንበት!

### CD 67

### Test Exercise 4b

ሰላም ቶማስ እንደምን ነህ? ሲኒማ ቤት መሄድ ትፈልጋልህ?
ማታ ሁለት ሰዓት ተኩል።
እሺ፤ ለሁለት ሩብ ጉዳይ?
እሺ። ጥሩ። ቻው።

## Chapter 10

### CD 68

### Exercise 3

| | |
|---|---|
| ባልደረባ፡ | ሰላም ዮሴፍ፣ ዛሬ ከሰዓት ቢሮ እመጣለሁ። አሁን ገና ሃዋሳ አየር ማረፊያ ነኝ። የበረራ ለውጥ አለ። |
| ዮሴፍ፡ | በረራህ ስንት ሰዓት ነው? |
| ባልደረባ፡ | አዲሱ በረራዬ ረፋድ 5 ሰዓት ላይ ነው። ልክ 12:30 አዲስ አበባ እደርሳለሁ። እባክህ ጠዋት ቢሮ እንደማልገባ ለአለቃዬ ንገርልኝ። አሁን የልስኬ ባትሪ ሊያልቅ ነው። ከሰዓት እንገናኝ።እሺ። |
| ዮሴፍ፡ | መልካም በረራ! |

### Exercise 5a and b

### CD 69/b

| | |
|---|---|
| ተጓዥ፡ | ሰላም ሊያ፣ አየር ማረፊያ መጥተሽ ትቀበይኛለሽ? |
| ሊያ፡ | ደስ ይለኛል። ስንት ሰዓት ትደርሳለህ? |
| ተጓዥ፡ | ማታ አንድ ሰዓት። |
| ሊያ፡ | አይ፤ ይቅርታ አልችልም። ማታ ጊዜ የለኝም። |

### CD 70/b

| | |
|---|---|
| ተጓዥ፡ | ሰላም ሊያ የበረራ ለውጥ አለ። |
| ሊያ፡ | በሌ ስንት ሰዓት ትደርሳለህ? |
| ተጓዥ፡ | ጠዋት አንድ ሰዓት እደርሳለሁ። ትቀበይኛለሽ? |
| ሊያ፡ | ደስ ይለኛል። እቀበልሃለሁ። |
| ተጓዥ፡ | እሺ አመሰግናለሁ። |

### CD 71

### Exercise 7b and c

1 ወደ ኢትዮጵያ መቼ ትበሪያለሽ?
የሚቀጥለው ሳምንት አርብ እበራለሁ።

2 አዲስ አበባ ስንት ሰዓት ትደርሻለሽ?
አርብ ጠዋት ሁለት ሰዓት እደሳለሁ።

3 ኤርፖርት መጥተህ ትቀበለኛለህ?
አዎ፣ ኤርፖርት መጥቼ እቀበልሻለሁ

4 ልክ አዲስ አበባ ስትደርሺ ትደውይልኛለሽ?
አዎ፣ አዲስ አበባ ስደርስ እደውልሀለሁ።

5 ብዙ ሻንጣ አለሽ?
አይ፣ ሁለት ሻንጣ እና አንድ የእጅ ቦርሳ ይዣለሁ።

6 በረራሽ ቀጥታ ነው?
አይ፤ በረራዬ ቀጥታ አይደለም። በኢስታንቡል ነው።

## Chapter 11

### CD 72

### Exercise 9a and b

| | |
|---|---|
| ወንድ 1፡ | ዛሬ ምን አደረክ? |
| ወንድ 2፡ | ዛሬ? ብዙ ነገር አላደረኩም። አነበብኩ። |
| ወንድ 1፡ | ምን አነበብክ? |
| ወንድ 2፡ | አንድ መጽሀፍ አነበብኩና ትንሽ አጠናሁ። |
| ወንድ 1፡ | አጠናህ? ምን  አጠናህ? |
| ወንድ 2፡ | አማርኛ አጠናሁና የቤት ስራ ሰራሁ። |
| ወንድ 1፡ | በጣም ጥሩ። |

### CD 73

### Exercise 11 b

ጥርሴን በጣም አሞኛል። እባክሽ፣ የጥርስ ክሊኒክ ስልክ ደውለሽ፣ ክፍት የስራ ሰዓት መቼ እንደሆነ ትነገሪኛለሽ? አመሰግናለሁ።

## Chapter 12

### CD 74

### Exercise 1

1 1587
2 2021
3 1518
4 414
5 1760
6 2050

### CD 75

### Exercise 5a

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | መስከረም | 6 | ሩጫ |
| 2 | እሮብ | 7 | ጥር |
| 3 | በረዶ | 8 | ቢራ |
| 4 | አርብ | 9 | ስራ |
| 5 | ክረምት | 10 | ቢራቢሮ |

### CD 76

### Exercise 5b

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዓመት | | | |
| ጸደይ | በጋ | መኸር | ክረምት |
| መስከረክም<br>ጥቅምት<br>ህዳር | ታህሳስ<br>ጥር<br>የካኪት | መጋቢት<br>ሚያዚያ<br>ግንቦት | ሰኔ<br>ሀምሌ<br>ነሃሴ ጳጉሜ |
| አዲስ ዓመት | ገና | ፋሲካ | ዝናብ |

## kïllä̈sa Chapter 10 - 12

### Exercise 3

### CD 77

ሰውዬ: ቀትር 6 ሰዓት ላይ እደርሳለሁ።
ሴትዮ: እንዴ። 6 ሰዓት ላይ ትደሳልሀ?
ሰውዬ: አሀ፣ ጉዞዋችንን 5:50 ላይ እንጀምራልን።
ሴትዮ: አሃ፣ ጉዞ 5:50 ትጀምራላችሁ!

### CD 78

### Exercise 4b

1 ትቀበለኛለህ?
2 የት ለምሳ እንቆማለን?
3 ታክሲ እንይዛለን?
4 ወደ ቢሮ በምን ትሄዳለህ?
5 ወደ ጅቡቲ የሚሄደው ባቡር ከየት ይነሳል?
6 አውሮፕላኑ አዲስ አበባ ስንት ሰዓት ይደርሳል?

## Fätäna 10 - 12

### CD 79

### Test Exercise 1

ሄኖክ: እንደምን አደርሽ ሄለን?
ኤደን: ደህና እግዜር ይመስገን! እንደምን አደርክ ሄኖክ?
ሄኖክ: ቅዳሜና እሁድ በደንብ አልተኛችሽም አይደል?
ኤደን: አዎ፤ በደንብ አልተኛሁም።
ሄኖክ: ቅዳሜ ጠዋት ልብስ አጠብኩና ቤቴን አጸዳሁ።
ኤደን: እኔ ጠዋት አስቤዛ አደረኩ።
ከሰዓት ጓደኛዬን ጸሀይን አገኘኋት። የፀሀይ ልደት ነበር። አንድ ላይ ካፌ ሄድንና ቡና ጠጣን። ከዛ ወደ ባር ሄድን። ከዛ ወደ ክለብ ሄድን። ብዙ ደነስን ቡዙ ጨፈርን።
ሄኖክ: ኧረባክሽ! ። እኔ ከሰዓት ስራ ሰራሁ።
ኤደን: በቅዳሜ ቀን! እረፍት አይደለም እንዴ?
ሄኖክ: ለሃኪም ቅዳሜን እሁድ እረፍት የለም። እሁድ ከሰዓት ግን እረፍት ነበረኝ። እሁድ ከሰዓት ጋዜጣ አነበብኩ፣ walk አደረኩ፣ በጣም ቆንጆ ነበር።
ኤደን: እሁድ አንድ ሰርግ ላይ የፎቶ ስራ ነበረኝ፣ ብዙ ፎቶ አነሳን። በጣም ጥሩ ሰርግ ነበር። ጥሩ ጊዜ አሳለፍን። አሁን ግን ደክሞኛል።
ሄኖክ: የሚቀጥለው ሳምትን እሁድ ጊዜ ካለሽ ትያትር ቤት መሄድ እንችላለን።
ኤደን: ደስ ይለኛል።

**Exercise 4b**

**CD 80**

1 ወደ ሃዋሳ መቼ ትሄዳለህ?
2 የት ለምሳ ትቆማላችሁ?
3 ነገ ትደውይልኛለሽ?
4 ወደ ህዋሳ የሚሄደው ባስ ስንት ሰዓት ላይ ይነሳል?
5 አዲስ አበባ ስንት ሰዓት ትደርሻለሽ?
6 እስከማይህ ጓጉቻለሁ።

**t'äč'ämari mälmäǧawočč**

**08 Exericse 9**

* *

**CD 81** - a

ሴትዮ፡ ኤልሳን ስንት ሰዓት ታገኛታለህ?
ሰውዬ፡ ስድስት ሰዓት ተኩል።

**CD 82** -b

ሴትዮ፡ ወደ ጂም ስንት ሰዓት ትሄዳለህ?
ሰውዬ፡ ለአንድ ሀያ አምስት ጉዳይ ላይ።

**CD 83** - c

ሴትዮ፡ ይቅርታ ! ባሱ ስንት ሰዓት ይነሳል?
ሰውዬ፡ አንድ ሰዓት ከአስር ላይ።

**CD 84** - d

ሴትዮ፡ ዳዊት፤ ስንት ሰዓት ትደርሳለህ?
ሰውዬ፡ ለስድስት ሃያ ጉዳይ ላይ እደርሳለሁ።

**CD 85** - e

ሰውዬ፡ ሰላም መቅደስ። ዛሬ ስንት ሰዓት ጊዜ አለሽ?
ሴትዮ፡ ለአራት ሩብ ጉዳይ ላይ ጊዜ አለኝ።

**CD 86** - f

ሰውዬ፡ አማርኛ ክላስ ስንት ሰዓት ይጀምራል?
ሴትዮ፡ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ይጀምራል።

* *

**CD 87**

1 ስንት ሰዓት ነው?
ለሁለት አምስት ጉዳይ።
2 አሁን ስንት ሰዓት ነው?
አስራ አንድ ሰዓት ከሩብ።
3 ስንት ሰዓት ነው
ለሶስት ሃያስምስት ጉዳይ።
4 ስንት ሰዓት ነው?
አራት ሰዓት ተኩል።